# የገጣሚ ያለህ!

ከታከለ ረታ

ጮማውና ጥሩው ተበልቶ ተጠቶ ፣
ታዳሚው እያገሳ አደራሹ ሙቆ፣
ሚያቀነቅን ጠፋ መች አጣ ከበሮ።

ለጠገበ በልቶ ግዳይ ለሸነጠው፣
ቆርጠጥ ቆርጠጥ ለሚል ምላጭ ለናፈቀው፣
ገጣሚ በቤቱ  አውራጅ  የለም ምነው?!

አታሞው ማሲንቆው፣ ክራሩ ዋሸንቱ፣
ነጋሪት በገናው ሁሉም በያይነቱ፣
አውራጅ እየጠራ ተስማምቶ ቅኝቱ
የት አለ ገጣሚው ድምጸ መዛሙርቱ?!

ድግስ ነው ካላችሁ የተጠራንበት፣
እንደ አባት-አደሩ ወሸባዬ እንድንል፣
ጎፈሬው እንዲታይ ወንዳወንድነት
በእልልታ እንዲያደምቁት የሴት ወዛዝርት፣
ጃሎ በል አቅራራ  ሽልል  ከፊት ቁመህ፣
ፎክር ተገማሸር አደባልቀው ገጥመህ!

ተበልቶ ተበልቶ ሁሉም ተጠጥቶ
ታዳሚ አንቀላፋ ትንፋሽ ድምጽ አጥፍቶ
ሰዓቱ  ሊያልፍ ነው ሊተኛ ቤት ገብቶ፣
ገጣሚ ከሌለ  ሚያስነሳው ነቅንቆ።

....///.....